የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፵፰
አዲስ አበባ ሚያዝያ ፱ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 48
ADDIS ABABA–17th April, 2003

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፳፰/፲፱፻፺፭ ዓ.ም
የንግድ ምዝገባና ፈቃድ (ማሻሻያ)
አዋጅ ........................................................ ገጽ ፪ሺ፩፻፶

## CONTENTS

Proclamation No. 328/2003
Commercial Registration and Business licensing (Amendment) Proclamtion ...................... Page 2150

### አዋጅ ቁጥር ፫፻፳፰/፲፱፻፺፭
### የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅን ለማሻሻል
### የወጣ አዋጅ

የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፷፯/፲፱፻፹፱ አንዳንድ ድንጋጌዎች በአፈፃፀም ላይ ችግር የታየባቸው በመሆኑ እና ለአዋጁም ተግባራዊነት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተጨማሪ ድንጋጌዎች ማካተት በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ–መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የንግድ ምዝገባና ፈቃድ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፫፻፳፰/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· <u>ማሻሻያ</u>

የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፷፯/፲፱፻፹፱ እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

፩· በአዋጁ አንቀጽ ፪ ሥር የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፳፮ እና ፳፯ ተጨምረዋል።

"፳፮· "የንግድ ረዳት" ማለት በንግድ ሕግ ከአንቀጽ ፵፬ እስከ አንቀጽ ፷፪ የተመለከቱት የንግድ ወኪሎች፣ ደላሎች እና ባለኮሚሲዮኖች ናቸው።"

"፳፯· "ተገቢ ያልሆነ የንግድ ሥራ" ማለት የንግድ አሠራር አዋጅ ድንጋጌዎችን የሚጥስ ማንኛውም ድርጊት ነው።"

### PROCLAMATION NO. 328/2003
### A PROCLAMATION TO AMEND THE COMMERCIAL REGISTRATION AND BUSINESS LICENSING PROLAMATION

WHEREAS, some provisions of the Commercial Registration and Business Licensing Proclamation No. 67/1997 have implementation difficulties; and it has been necessary to include some additional provisions that are relevant for the implementation of the proclamation.

NOW, THEREFORE, In accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratice Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

1. *Short Title*

This proclamation may be cited as "Commercial Registration and Business licensing (Amendment) Proclamation No. 328/2003."

2. *Amendment*

The Commercial Registration and Business Licensing Proclamation No. 67/1997 is hereby amended as follows.

1) the following new Sub–Articles (26) and (27) are added under Article 2 of the Proclamation.

"26. "Trade Auxiliary" means Commercial agents, Commercial brokers and Commission agent prescribed under Articles 44 up to 62 of the Commercial Code."

"27. "Unfair Trade Practice" means any activity which violates the provisions of Trade Practice Proclamation."

ያንዱ ዋጋ 2.30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· በአዋጁ አንቀጽ ፫ ሥር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተጨምሯል።
"፬· በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም፣ በቡና፣ በቆዳና ሌጦ፣ በጫት እና ሚኒስቴሩ ፈቃድ ያስፈልጋቸዋል ብሎ በሚያምን ባቸው የውጭ ንግድ እቃዎች የንግድ ሥራዎች ላይ ለመሰማራት የንግድ ሥራ ፈቃድ መውጣት ግዴታ ነው።"

፫· በአዋጁ አንቀጽ ፲፬ ላይ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፰) ተጨምሯል።
"፰· በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፭ በንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት የንግድ ስም በመዝገብ ከመግባቱ በፊት ስሙን ሌላ ሰው በንግድ ስም መዝገብ ወይም በንግድ ዋና መዝገብ ያላስገባው መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል።"

፬· በአዋጁ አንቀጽ ፳፩ ላይ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተጨምሯል።
"፫· የንግድ ሥራ ፈቃድ በስሙ የተሰጠው ድርጅት በፍርድ ቤት እንዲፈርስ ሲወሰንበት የተሰጠው የንግድ ሥራ ፈቃድ የፀና ሆኖ አይቆጠርም።"

፭· በአዋጁ አንቀጽ ፳፩ የቀድሞዎቹ ንዑስ አንቀጽ (፫)፣ (፬) እና (፭) እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጽ (፬)፣ (፭) እና (፮) ሆነዋል።

፮· የአዋጁ አንቀጽ ፳፰ ንዑስ አንቀጽ (፬) ውስጥ "አዲስ ተመሳሳይ ፈቃድ" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "ያንኑ የንግድ ሥራ ፈቃዱ እንደ አዲስ" በሚለው ተተክቷል።

፯· በአዋጁ አንቀጽ ፳፰ ላይ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፮) ተጨምሯል።
"፮· በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፬) የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም የንግድ ሥራ ፈቃዱ የተሰረዘበት ነጋዴ ፈቃዱ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ ባሉት ፷ ቀናት ውስጥ ፈቃዱን ተመላሽ ካላደረገ ያንኑ የንግድ ሥራ ፈቃድ እንደ አዲስ ለማውጣት የሚችለው ፈቃዱ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ ከሁለት ዓመት በኋላ ነው።"

፰· በአዋጁ አንቀጽ ፴ የነበረው ድንጋጌ አንቀጽ (፩) ሆኖ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተጨምሯል።
"፪· የንግድ ድርጅት በማንኛውም ሕጋዊ መንገድ ለሌላ ሰው ሲተላለፍ የንግድ ድርጅቱ በተላለፈለት ሰው ወጭ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ ይደረጋል።"

፱· የአዋጁ አንቀጽ ፴፪ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፴፪ ተተክቷል።
"፴፪· ቋሚ የግብርና ልማት ወይም የኢንዱስትሪ ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ምርቱን በጅምላ ለመሸጥ ወይም ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ የጅምላ ወይም የላኪነት ፈቃድ እንዲያወጣ አይገደድም።"

፲· የአዋጁ አንቀጽ ፴፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል።
"፩· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳ ንዑስ አንቀጽ (፬) እና (፭) መሠረት መመሪያ ያዘጋጁ ወይም የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የሰጡ የሴክተር መሥሪያ ቤቶች የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጠባቸው ግዴታዎች መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው።"

፫· **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከሚያዝያ ፱ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፱ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት



2) The following new Sub-Article (4) is added under Article 3 of the Proclamation.
"4. "Notwithstanding the provisions of Sub–Article (2) of this Article it is compulsory to obtain business license for commercial activities such as coffee, skin and hide, chat and other foreign trade goods for which the Ministry deems business license is necessary."

3) The following new Sub-Article (8) is added under Article 14 of the Proclamation.
"8. Before effecting entry of a trade name in a register pursuant to Sub-Article (5) of Article 5 of this Proclamation, it shall be ascertained that such a name is not entered either in a trade name register or commercial register by any other person."

4) The following new Sub-Article (3) is added under Article 21 of the Proclamation.
"3. A Business license obtained by the business organization shall not be considered valid, if dissolved by the order of court."

5) The formers Sub-Articles (3), (4) and (5) of Article 21 of the Proclamation are renumbered as Sub-Articles (4), (5) and (6) respectively.

6) The phrase "a similar license." appearing in Sub-Article (4) of Article 28 is deleted and replaced by the phase "the same business license as new."

7) The following new Sub-Article (6) is added under Article 28 of the Proclamation.
"6. Notwithstanding the provisions of Sub–Article (4) of this Article, a business person whose license is canceled may obtain the same license as new after two years, if he fails to return his license within 60 days after his license is canceled."

8) Existing provision under Article 30 is numbered as Sub-Article (1), and the following new Sub-Article (2) is added under Article 30.
"2. Where any business is legally transferred to any other person, a notice to this effect shall be published in a newspaper at the expense of the transferee."

9) Article 32 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 32.
"32. Any person who has a permanent license for agricultural development or industry shall not be required to obtain wholesale or export business license in order to wholesale or export his products."

10) Sub-Article (1) of Article 35 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (1).
"1. Relevant sectoral government organs who issued directives or evidence of professional qualifications or certificates of competence pursuant to Sub-Articles (4) and (5) of Article 20 of this Proclamation, shall have an obligation to conduct follow-up and inspection work in order to insure the observance of the conditions for which any business license is given."

3. *Effective Date*

These Proclamation shall enter into force as of the 17th day of April, 2003.

Done at Addis Ababa 17th day of April, 2003.

GIRMA WOLDE GIORGIS

PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE